# ለሸማቾች የተሰጠ ማስጠንቀቂያ

## የ Pepco የደንበኞች ዝቅተኛ የክፍያ ተመን በዚህ ሳምንት ይጠናቀቃል
## *የመኖሪያ ቤት የኤሌክትሪክ ፍጆታ ክፍያዎች ይጨምራሉ*

## ፌብሩዋሪ 17, 2021

የደንበኞች ዝቅተኛ የክፍያ ተመን (CBRC) በዚህ ሳምንት የሚያበቃ በመሆኑ፣ የኤሌክትሪክ ክፍያዎች የሚጨምሩ መሆኑን የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የህዝብ ምክር ቤት ጽ/ቤት ለ Pepco ሸማቾች ለማሳሰብ ይወዳል።

CBRC እንደ Pepco-Exelon ውህደት የስምምነት አንድ አካል ሆኖ የቀረበ እና OPC ለመኖሪያ ቤት ተጠቃሚዎች ያሸነፈው ጥቅማጥቅም ነው። CBRC ላለፉት 5 ዓመታት የመኖሪያ ቤት የፍጆታ ክፍያዎች የስርጭት ክፍል ላይ የነበረን የጭማሪ መጠን ለማካካስ አገልግሎት ላይ ሲውል ነበር። ባለፉት 5 ዓመታት ውስጥ ከተጠቃሚዎች ሊቀር የቻለው የተጣራ ቁጠባ $25.6 ሚሊዮን ዶላር ነው። ነገር ግን፣ አሁን የድጋፍ ገንዘቡ በመጠናቀቁ ምክንያት Pepco የደንበኞችን የክፍያ መጠን በማስተካከሉ ከአሁን ሰዓት ጀምሮ ጭማሪዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ እያደረገ ነው። ይህም ማለት፣ በመጪው የክፍያ መጠየቂያ ዙር ላይ አማካይ የመኖሪያ ቤት የኤሌክትሪክ ፍጆታ በወር በ $1.37 ዶላር ያህል ከፍ ይላል ማለት ነው።

ከፍተኛ የሆነ የኤሌክትሪክ ክፍያ የ COVID-19 ወረርሽኝ ባስከተለው ቀውስ ምክንያት የኑሮ ጫና ለደረሰባቸው ቤተሰቦች የበለጠ የገንዘብ ጫና ሊያስከትልባቸው እንደሚችል OPC በሚገባ ይገነዘባል። በመሆኑም፣ OPC ወረርሽኙ ከተከሰተበት ጊዜ አንስቶ ሸማቾች ከነበሩት የእርዳታ ፕሮግራሞች እና የክፍያ እቅዶች በአግባቡ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሲያበረታታ ቆይቷል። በአሁኑ ወቅት፣ የፍጆታ አገልግሎት አቅራቢዎች ክፍያዎች ባለመፈጸማቸው ምክንያት የፍጆታ አገልግሎቶችን እንዳያቋርጡ የዲስትሪክቱ የህብረተሰብ ጤና የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ይከለክላል። ሆኖም ግን፣ እገዳዎቹ ሲነሱ ከአቅም በላይ የተጠራቀመ ክፍያ እንዳይኖርባቸው ለማስቻል ሸማቾች አሁን መክፈል የሚችሉትን አሁኑኑ እንዲከፍሉ፣ ለመገልገያ ፍጆታ የገንዘብ ድጋፍ ፕሮግራሞች ብቁ መሆን እና አለመሆናቸውን እንዲያረጋግጡ፣ እና ለክፍያ ዕቅዶች እንዲመዘገቡ OPC ያበረታታሉ።

ስለ አገልግሎት ክፍያ ድጋፍ የበለጠ ለማወቅ፣ በስልክ ቁጥር (202) 727-3071 ወይም በኢሜይል info@opc-dc.gov OPCን ያነጋግሩ።